# Global Coalition for Lake Tana Restoration

Address: 4600 14th St. NW, Washington DC 20011
United States
Tel: +1 949 299 8473
Email: management@tanacoalition.org
Website: www.tanacoalition.org

---

Date: 09/21/2018

## Update on the machines

**የተገዛውን ማሽን በተመለከተ**

ከዚህ በፊት በአትላንታና በእስራኤል በተደረጉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ድጋፎች ተገዝቶ ሃገር ውስጥ የገባውን የእንቦጭ ማጨጃ ማሽንን በተመለከተ ያሉ ብዥታዎችን ማጥራት ተገቢ ነው። በመጀመሪያ ማሽኑን ከመግዛታችን በፊት በቂ ጥናት ተደርጎ ነው ወደ ስራ የተገባው። ጥናቱም በጣና ላይ ያለውን የእንቦጭ ስርጭት፤ አካባቢያዊ ባህርይ፤ የውሃ ጥልቀትና ባዮፊዚካላዊ ባህርይን የዳሰሰና እነዚህን ባህርዮች በመጠቀም የሚያስፈልጉ የማሽንና ሌሎች እንቦጭን የመከላከል ዘዴዎች የለየ ነው። ጥናቱ እንደሚያመለክተው በመስከረም 2017 እ.ኤ.አ 5,349 ሄክታር የእንቦጭ ሽፋን በ18 ቀበሌዎች እንደሚገኝ ያመለከተ ሲሆን፤ የእንቦጩ ስርጭትም ሶስት አይነት ነው - 6 ቀበሌዎች አነስተኛ የእንቦጭ ስርጭት ያላቸው (ከ100 ሄክታር በታች የአረም ሽፋን ያላቸው)፤ 5 ቀበሌዎች መካከለኛ የእንቦጭ ስርጭት ያላቸው (ከ100-200 ሄክታር የአረም ሽፋን ያላቸው)፤ እንዲሁም 7 ቀበሌዎች ከፍተኛ የእንቦጭ ሽፋን ያላቸው (ከ200 ሄክታር በላይ) ነበር። የውሃ ጥልቀቱም፤ አነስተኛና መካከለኛ የእንቦጭ ስርጭት ያላቸው ቦታዎች 0.3-0.8ሜ ሲሆን፤ ከፍተኛ የእንቦጭ ስርጭት ያላቸው ቦታዎች ደግሞ ከ0.8ሜ በላይ ነበር። አረሙ በየቀኑ ተለዋዋጭ ባህሪ (temporal variation) ስላለው ከመስከ ጥናቱ በተጨማሪ የእያንዳንዱን ወር የእንቦጭ ስርጭት ከሳተላይት ምስል በመውሰድ፤ በተለያዩ ወቅቶች (seasonally) ያለውን ተቀያያሪ ባዮፊዚካል መረጃዎችና የአረሙን ስርጭትን  በሚገባ ዳሷል። ይህም የእንቦጭን ስርጭት ዳይሬክሽንና የሃይቁን ተለዋዋጭ የውሃ ጥልቀትን እንድናውቅ ረድቶናል። ይህ ሳይንሳዊ ስራ ሃይቁ ላይ የሚካሄደውን የእንቦጭ እንቅስቃሴ ከመረዳትም ባሻገር በክረምትና በበጋ አረሙን ለማስወገድ መሰራት ያለባቸውን ስራዎችና ቦታዎችን ለመለየት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። ጥናቱ ለእንቦጭ መስፋፋት ተጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎች (environmental factors) (የውሃ ሞገድና ሌሎች አካባቢያዊ ባህርያት) በአነስተኛና መካከለኛ የእንቦጭ ሽፋን ባላቸው ቦታዎች ላይ እንደሚበረታ አመላክቷል። (በነዚህ ቦታዎች በመስከረም ወር አረሙ በቀን በአማካኝ 6-8 ሄክታር ድረስ ጭማሪ ሲያሳይ፤ በተቃራኒው ከፍተኛ የእንቦጭ ሽፋን ባለባቸው ቦታዎች  ግን በቀን ከ1-2 ሄክታር በላይ ጭማሪ አላሳየም [ይህም saturation stage ላይ መድረሱን ያሳያል]) - በዚህ መረጃ መሰረት እንቦጩ በከፍተኛ ሁኔት እየተሰራጨ ያለው አነስተኛና መካከለኛ የአረም ሽፈን ባለባቸው አካባቢዎች (የሃይቁ ምስራቃዊ ዳርቻዎች) መሆኑን ያመላከታል። በማንኛውም አረም ቁጥጥር ስራ የመጀመሪያው ቀዳሚው ተግባር የአረሙን ስርጭት መግታት ነው። በዚህም መሰረት የእንቦጩን ስርጭት ለመግታት ቅድሚያ ሰጥቶ መሰራት ያለበት ቦታ አነስተኛና መካከለኛ የእንቦጭ ሽፋን ያላቸው ቦታዎች መሆን እንዳለበት አሳይቷል። ለምሳሌ፤ በእነዚህ በአነስተኛና መካከለኛ የእንቦጭ ሽፋን ያላቸው ቦታዎች አጎራባች የሆኑ ሁለት ቀበሌዎችን በአንድ ወር ውስጥ እንቦጩ አዳርሷቸው ነበር። ስለዚህ የመጀመሪያው ማሽንን ስንገዛ

# Global Coalition for Lake Tana Restoration

Address: 4600 14th St. NW, Washington DC 20011
United States
Tel: +1 949 299 8473
Email: management@tanacoalition.org
Website: www.tanacoalition.org

---

አላማው አነስተኛና መካከለኛ የእንቦጭ ሽፋን ያለባቸውን 11 ቀበሌዎች ላይ ውጤት ማምጣት የሚችል መሆን አለበት የሚል ነበር። እነዚህ ቀበሌዎች የውሃ ጥልቀታቸው አነስተኛ (በአማካይ 0.4ሜ) በመሆኑ የሚገዛው ማሽን መካከለኛ ክብደት ያለውና አነስተኛ ጥልቀት ላይ መስራት የሚችል መሆን ነበረበት ማለት ነው። ይህም ማለት ከፍተኛ ክብደትና ጉልበት ያላቸው ማሽኖች ለመንቀሳቀስ ከ0.8ሜ ጥልቀት በላይ ስለሚፈልጉ በነዚህ 11 ቀበሌዎች ላይ ምናልባት በክረምት ወቅት ካልሆነ በቀር ዓመቱን ሙሉ ለመስራት ይቸገራሉ። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት የገዛነው ማሽን ይህንን የሚያሟላ ነው- በአነስተኛና መካከለኛ የእንቦጭ ሽፋን ባለበት ቦታ መስራት የሚችልና ለመስራት የሚፈልገው አማካይ የውሃ ጥልቀትም 0.4ሜ በመሆኑ። ይህም በ11ዱ መካከለኛና አነስተኛ የእንቦጭ ሽፈን ባላቸው አካባቢዎች ያለውን የእንቦጭ መጠንና ስርጭት በመቀነስ አረሙ ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዳይዛመትና ኮንቴይን ለማድረግ ያግዛል ማለት ነው። አንዳንዶቹ እነዚህ አካባቢዎች ከማሽን በተጨማሪም የሰው ሃይል በማስገባት ከፍተኛ ስራ የሚሰራባቸው ናቸው - በዚህም አበረታች ለውጥ ታይቷል (ከታች የተያያዘውን ምስል ተመልከቱ)::

የመስክና የሳተላይት መረጃዎችን በማጠናከር ከተደረገው ጥናት በተጨማሪ ቀደም ብሎ የገባ የአማጋ ማሽን (በግል ባለሃብት ከቻይና ተገዝቶ የመጣ) የመስክ ግምገማ (evaluation) ተደርጎ ነበር። የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን ያቋቋሙት ሃገር በቀል ማህበር (የጣና ተፋሰስ የተቀናጀ በጎ አድራጎት ማህበር) ጋር በመተባበር የማሽኑን የመስክ ስራ ኢቫሉየት በማድረግ የታዩ ክፍተቶችን በቀጣይ የማሽን ግዥ ላይ እንዳይከሰቱ ትምህርት ተወስዷል። ጥናቱ የማሽኑን አረም የማጨድ ካፓሲቲ፣ ኦፐሬሽን፣ የአረም አወጋገድ (post-harvest)ና የጥገና አሰራር (maintenance) በሚገባ ዳሷል። የጥናቱ ሪፖርት ከዚህ ኢሜል ጋር ተያይዟል።

በአጠቃላይ በነዚህ የጥናት ውጤቶች ላይ በመንተራስ የማህበራችን የሳይንቲፊክ ቡድን ከሃይቁ ባህርያት ጋር የተጣጣመ የማሽን ስፔስፊኬሽን በማውጣት በዓለም ዙርያ ካሉ የማሽን አምራቾች የምንፈልገውን የማሽን አይነት በማስረዳት የሚያመርቷቸውን የአረም ማጨጃ ማሽኖች ስፔስፊኬሽኖችና ዋጋ በመሰብሰብ ኢቫሉየት ተደርጓል። እዚህ ላይ የተጠቀምንበት የመመዘኛ criteria የሚከተሉት ነበሩ፤ 1) ከዚህ በፊት በተለያዩ ሃገሮች (በተለይ በአፍሪካ መልክአምድር) ተሞክሮ ጥሩ ውጤት ያመጣ፤ 2) በቂ መለዋዋጫ ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ የሚችል (ከአማጋው ማሽን የተማርነው አንዱ ተግዳሮት በቂ መለዋወጫ ባለመቅረቡ የማሽኑ ጥገና ብዙ ጊዜ ይወስድ ነበር)፤ 3) ማሽኑን ኦፐሬት ለማድረግ ከፍተኛ ባለሙያ የማይጠይቅ (User friendly የሆነ)፤ 4) የጥገና ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነና በሃገር ውስጥ ባለሙያ ሊሰራ የሚችል፤ 5) ኦፐሬሽናል ኮስቱ አነስተኛ የሆነ (cost-effective)፤ 6) ቢያንስ የ2 ዓመት ዋራንቲ (warranty) ያለው፤ 7) የማሽኑን አጠቃቀም ስልጠና መስጠት የሚችል፤ 8) ለማጓጓዝ አመቺ የሆነ (ቢቻል አሴምብልድ የሆነ)ና፤ 9) የማሽኑ ዋጋ በእጃችን ከነበረው ፈንድ ($62,500) ጋር ተመጣጣኝ የሆነ። በዚህ መሰረት በቻይና፣ ታይላንድ፣ አውስትራሊያ፣ ጀርመንና ካናዳ

Address: 4600 14th St. NW, Washington DC 20011
United States
Tel: +1 949 299 8473
Email: management@tanacoalition.org
Website: www.tanacoalition.org

---

የሚገኙ የአረም ማጨጃ ማሽን አምራቾችን አወዳድረናል። በመጨረሻም ያስቀመጥናቸውን ቅድመ ሁኔታዎችን በአብዛኛው በሚሟላት የካናዳውን H5-200 የእንቦጭ ማጨጃ ማሽን ገዝተናል።

ማሽኑ ተልኮ ኢትዮጵያ ሲደርስ ሁለት የማህበራችን ከፍተኛ ባለሙያዎች በራሳቸው ወጭ ኢትዮጵያ በመሄድ የማሽኑን አጠቃቀምና ጥገና ለባለሙያዎች ስልጠና ሰጥተዋል። ጣና ላይ የሙከራ ስራ ተሰርቶ ሙሉ ለሙሉ በጥሩ አቋም ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ለክልሉ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስረክበናል። በሰኔ ወር ደግሞ እኔ ኢትዮጵያ የመሄድ እድሉ ስለነበረኝ የባለሙያዎች ቡድን (ከክልሉ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ; ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲና ኢንጂነር ሙላት ባሳዝነው ጋር በመሆን) የመስክ evaluation ሰርተናል። ማሽኑ ምንም ችግር እንደሌለበትና እንዲሰራ በተወሰነለት ቦታ ላይ ብቻ ማሰራት እንደሚገባ ግብረ-መልስ (feedback) ተሰጥቷል። የኛ ማህበር ማሽኑን ለቢሮው አስረክቧል፤ ስለዚህ ማሽኑን ተቆጣጥሮ ማሰራት ያለበት የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ ነው። የማሽኑ ባለቤት የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ እንደመሆኑ አስፈላጊውን ሎጂስቲክስ በመመደብ የቀንከቀን ስራዎችን በማቀድና በመከታተል፤ ማስፈጸም ይጠበቅበታል።

**በቀጣይ የሚገዙ ማሽኖች**

አሁን ለመግዛት እንቅስቃሴ እያደረግን ያለነው ማሽን ደግሞ ከፍተኛ የአረም ሽፋን ያለባቸውን አካባቢዎችን ስነምህዳራዊ ባህሪ ያገናዘበ ከፍተኛ የፈረስ ጉልበት ያለውና ጥልቀት ባለው ውሃ ላይ (>0.8ሜ) የሚሰራ ነው። እስካሁን ካወዳደርናቸው ውስጥ ዓለም አቀፍ ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ እጅግ ጠንካራ (ረጅም እድሜ መቆየት የሚችሉ)ና ግዙፍ ማሽኖች ዋጋቸው ውድ በመሆናቸው በሌሎች ቦታዎች ገንዘብ ከሰበሰቡ አካላት ጋር በመቀናጀት ትልቅ comprehensive ማሽን (ሶስት ኮምፖነንቶች ያሉት - መሰብሰብ፤ መጭመቅና መፍጨት የሚችል መልቲ-ታስክ ማሽን) አስበን ነበር። ነገር ግን ሌሎች ቡድኖች ተባባሪ ባለመሆናቸው ሳይሳካ ቀርቷል። ስለዚህ ያለን አማራጭ ባለን ገንዘብ (ዲሲናቺካጎ የተሰበሰበውን፤ እንዲሁም በለንደንና ኔዘርላንድ የተሰበሰበውን [ገና ያልተረከብነው ነው] ጨምሮ) አንድ ትልቅ ማሽን ለመግዛት በሂደት ላይ ነን። ለአፍሪካ ትልልቅና አስተማማኝ ማሽኖችን በማቅረብ የሚታወቀው Aquarius Systems ኢትዮጵያ ድረስ በመሄድ የጣናን ወቅታዊ ሁኔታ ተመልክቷል። ከክልሉ አካባቢ ባለስልጣንና ከእኛም ጋር በስፋት ስለጣና ecosystem ተወያይቷል። የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ ባለሙያዎች ማላዊ ድረስ ሄደው 13 ዓመት ሙሉ እየሰራ ያለ ማሽን አይተዋል (የባለሙያዎቹ የመስክ ሪፖርት ከታች ተያይዟል)። የማሽኑን አጠቃቀምና የአረሙን አወጋገድ በተመለከተ ከማላዊ ባላሙያዎች ጋር በስፋት ተወያይተዋል። ይህ ማሽን በኬንያ፤ ዩጋንዳ (የቪክቶርያ ሃይቅ)፤ በካሜሩን፤ ደቡብ አፍሪካና ሌሎች አፍሪካ ሃገራት በስፋት ተጠቅመውበታል። የማሽኑ ሞዴል 820 Series የሚባል ሲሆን (ከታች ፎቶው ተያይዟል)፤ 75 የፈረስ ጉልበት ያለውና በአንዴ 23.2 ሜትር ኪውብ (7,076 ኪሎግራም) እንቦጭ መሸከም ይችላል። ሁለት መካከለኛ ማሽን ከመግዛት አንድ ትልቅ አቅም ያለው ማሽን በመግዛት ከፍተኛ የእንቦጭ ሽፋን ባለው ቦታ የምንፈልገውን ውጤት በአጭር ጊዜ ለማየት ያስችላል ብሎ የማህበራችን

Address: 4600 14th St. NW, Washington DC 20011
United States
Tel: +1 949 299 8473
Email: management@tanacoalition.org
Website: www.tanacoalition.org


---

የሳይንቲፊክ ቲም ወስኗል። አምራቹም ከ50 ዓመት በላይ የእንቦጭ ማሽን በማምረት በዓለም ዙርያ አቅራቢ የሆነው አኳሪየስ ሶሉሽንስ (Aquarius Solutions) ነው - ፋብሪካው የሚገኘው በዊስኮንሰን ግዛት ነው። ዋጋውም $222,170 ዶላር ነው። የማሽኑ አምራች ማሽኑን አምርቶ ለማስረከብ አራት ወራት እንደሚፈጅ ገልጾልናል። ጣና ድረስ በመሄድ ማሽኑን ቴስት አድርጎ፤ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ነው የሚያስረክበን። በቂ መለዋወጫም ያቀርባል። የጣናን ባህርይ ቦታው ድረስ ሄደው ስላዩ የማሽኑ ስፔስፊኬሽንን ለጣና ተስማሚ ለማድረግ ረድቷል። ከዚህ ቀደም እንዳደረግነው የኢትዮጵያ መርከቦች ድርጅት ማሽኑን በነጻ እስከ ጅቡቲ ወደብ ያደርስልናል ብለን እንተማመናለን። በቀጣይም የስራውን እንቅስቃሴ ለህዝብ እናሳውቃለን።

በአጠቃላይ የተከተልነው የአረም አወጋገድ አሰራር መጀመሪያ የእንቦጩ ሽፋን አነስተኛና መካከለኛ የሆኑ ቦታዎችን ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር እንቦጩ ወደሌሎች ቀበሌዎች የመዛመት ስርጭት መቀነስና መቆጣጠር ነው። ቀጥሎ አረሙ ሳቹሬት ባደረገበት ቦታዎች ላይ የተቀናጀ የአረም አወጋገድ በመከተል intensively መስራት ይሆናል። ባንዴ ሁሉንም አይነት ማሽኖች ለማቅረብ አቅም የለንም። የማሽኑ አይነት ሊሰራ እንደታሰበው ስራ፤ እንደ አካባቢው ባህሪ፤ እንደ ውሃው ጥልቀትና እንደ አዋጭነቱ ይወሰናል። One-fits-all አይነት ማሽን የለም። ዋናው ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ደግሞ እኛ ብቻ የምናደርገው ድጋፍ ለጣና በቂ ነው የሚል እምነት የለንም። በዋናነት ሃላፊነቱን መወጣት ያለበት መንግስት ነው፤ እኛ ከህብረተሰቡ በምንሰበስበው ውስን ፈንድ ክፍተት ያለባቸው ስራዎችን ብቻ ነው ማገዝ የምንችለው።

**ማጠቃለያ**

ዓለማቀፉ ጣናን መልሶ ማቋቋም ማህበር ወደ ስራ ከገባበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአጭር ጊዜ ብዙ ስራዎችን ከውኗል። 1) የተለያዩ ጥናቶች አካሂደናል፤ ይህም የእንቦጩን ባህሪ፤ ቁጥጥርና አወጋገድ ላይ ግንዛቤ ፈጥሯል። 2) ባለሙያዎች የራሳቸውን ወጭ በመሸፈን በተለያየ ጊዜ ወደ አካባቢው በመጓዝ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ ባለሙያዎችንን አሰልጠነዋል። 3) የመስክና የሳተላይት መረጃዎችን በማጠናከር የእንቦጭ ስርጭት ዲጂታል ካርታ ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጅቶ፤ በመረጃ የተደገፈ ስራ እንዲካሄድ አስተዋጾ አድርገናል። 4) እንቦጭን በተመለከተ ሃገር-አቀፍና ዓለም አቀፍ ገንዛቤ የማስጨበጥ የኮሚኒኬችንና የመረጃ (awareness creation and information dissemination) ስራዎች ሰርተናል። 5) ከፌደራል አካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር መስሪያቤት ጋር በመተባበር ስራው በዕውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ ሃላፊ ፍሎሪዳ (በዓለም ላይ effective water hyacinth control system አላቸው ከሚባሉት ቦታዎች ቀዳሚ ነው) ላይ የሚሰራውን የእንቦጭ አወጋገድ ስራ እንዲያዩ፤ ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር እንዲመካከሩና ትምህርት እንዲወስዱ ተደርጓል። 6) የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እያካሄደ ያለውን የባዮኮንትሮል ሙከራ፤ ከሙከራ ወደተግባር እንዲገባ ድጋፍ እያደረግን ነው (በቅርቡም የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፤ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩትና የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች የሚስተፉበት የባዮኮንትሮል ስልጠና በዩጋንዳ ይካሄዳል - ይህም ስራውን ከሙከራ ወደ ተግባር የሚያሸጋግር የትግበራ

Address: 4600 14th St. NW, Washington DC 20011
United States
Tel: +1 949 299 8473
Email: management@tanacoalition.org
Website: www.tanacoalition.org


ማንዋል (implementation manual) ለማዘጋጀት ይረዳል)፤ 7) የአምስት አመት ጣናን ከእንቦጭ የመቆጣጠርና ተፋሰሱን መልሶ የማቋቋም ስትራቴጂክ ዶክመንት ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ቴክኒካል አስተዋጾ አድርገናል፤ 8) በግንቦት ወር አንድ ማሽን በማስገባት በማሽን የታገዘ ስራ እንዲሰራ የድርሻችንን አበርክተናል; 8) የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) በቅርብ ባከሄደው ጣናን ከእንቦጭ ለመታደግ የሚመክር ስብሰባ ላይ በመገኘት የጥናት ውጤቶቻችንን በማቅረብና ምን ምን ሊሰራ እንደሚገባ በዝርዝር በማስረዳት UNEP ሊያዘጋጀው ባሰበው ፕሮፖዛል የሚጽፍ ኮሚቴ ውስጥ የድርሻችንን ለማገዝ ጥረት እያደረግን ነው። [የማህበሩ የአንድ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት በታች በሰንጠረዥ ተቀምጧል]

በመጨረሻም ዓለማቀፉ ጣናን መልሶ ማቋቋም ማህበር እንደ አንድ ባለድርሻ ማህበር የራሱን ድርሻ እየተወጣ ቢሆንም ጣናን የማዳን ተግባር ግን በመንግስት ወጥ የሆነ ከፍተኛ ትኩረት ይሻል። በተለይ ጣናን የሚያስተዳድር ራሱን የቻለ ተቋም ሊቋቋም ይገባል። ይህ ሲሆን ነው ጣና ላይ በዘላቂነት የሚሰሩ ስራዎች ባለቤት ኖሯቸው ዘላቂ ለውጥ የሚመጣው ብለን እናምናለን።

| **Annual financial report – [Sept 2017-Sept 2018] Global Coalition for Lake Tana Restoration** | | |
|---|---|---|
| **Items** | **Description** | **USD** |
| Funds raised | Atlanta, Israel, DC, Chicago, New Zealand and Online fundrasings | 277,995 |
| Harvesting Machines Purchased | One machine purchased and delivered | -67,290 |
| Harvesting machine ordered | One machine with conveyer ordered (down payment paid) | -37,000 |
| Trainings | International and local trainings for Regional Env. Authority experts | -2,250 |
| Assessment, Monitoring and Evaluation | Field assessments and M&E surveys conducted around Lake Tana in collaboration with Charitable Organization for Integrated Lake Tana Basin Development (COILTBD) | -2,500 |
| Expenses to conduct fundraisings | Printings, entertainment, hall rentals etc | -14,910 |
| Current balance as of 21 Sept 2018 | | **154,045.00** |

For timely updates please follow our website: www.tanacoalition.org
Facebook page: https://www.facebook.com/groups/837333129767209/

ዓለማቀፉ የጣና መልሶ ማቋቋም ማህበር